Arlington2050
Guiding Our Path
Arlington County's Comprehensive Plan Update

**COMPREHENSIVE PLAN UPDATE PROJECT**
**Guiding Principle Mini-Series**

# ሁሉን አቀፍ የእቅድ ማሻሻያ ፕሮጀክት፡ የመመሪያ መርህ ትኩረት

ዛሬ ወደ ሁለቱ የአሜሪካ የእቅድ ማህበር የመመሪያ መርሆች እየገባን ነው፡ **የተጋመደ እኩልነትና ጤናማና ደህንነቱ የተጠበቀ ማህበረሰብ**

ሁሉም ሰው በማህበረሰቡ ውስጥ እድል፣ ጤናን እንዲሁም ደህንነት ሲያገኝ እያበበ ይሄዳል፡፡ አርሊንግተን ፍትሃዊ፣ ጤናማና ለሁሉም ሰው ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን እንዴት እናደርጋለን?

የአሜሪካ የእቅድ ማህበር
የመመሪያ መርሆች፡

## የተጋመደ እኩልነት

*ለሁሉም ዜጎችና ቡድኖች የመኖሪያ ቤት፣ አገልግሎት፣ ጤና፣ ደህንነትና መተዳደሪያ ፍላጎቶችን በማቅረብ አኳያ ፍትሃዊነትንና እኩልነትን ማረጋገጥ፡፡*

በማህበረሰብ ውሳኔዎችና አገልግሎቶች ውስጥ እኩልነት ማለት ጥቅሞችና ወጪዎችን በፍትሃዊነት መጋራት ማለት ነው፡፡ ይህ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለ ማንኛውም ግለሰብ - ሀብታምና ድሀ፣ ወጣትና አዛውንት፣ ተወላጅና ስደተኛ - ፍላጎት መሟላቱን ለማረጋገጥ ቁልፍ ጥያቄዎችን መጠየቅን የሚያካትት ነው፡፡ እንደ ወጣቶችና ስደተኞች ያሉ ተጎጂ የሆኑ ቡድኖች በማህበረሰብ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ላይ በሚካሄዱ ውይይቶች ላይ የማይሳተፉ ሲሆን ይህም ፍላጎቶቻቸውን ችላ እንዲሉ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ድሆችና አናሳ ቁጥር ያላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች አብዛኛውን ጊዜ በብክለትና በተፈጥሮ አደጋዎች ከፍተኛ ጉዳት ይደርስባቸዋል፡፡ እነዚህ ቡድኖች ለስራ፣ ለሃብትና ለጤና አጠባበቅ አስፈላጊ የሆኑ ክህሎቶች ወይም የማህበረሰብ ግንኙነቶች ላይኖራቸው ስለሚችል ማህበረሰቡ እነሱን ለመርዳት ልዩ ፕሮግራሞችን መፍጠር ይጠበቅበታል፡፡ ተመጣጣኝ መኖሪያ ቤት በዚህ መርህ ስር የሚገኝ ሌላኛው አስፈላጊ የፍላጎት ክፍል ነው፡፡ የእኩልነት ግምትን በአጠቃላይ እቅድ ውስጥ በማካተት ማህበረሰቡና መሪዎቹ ፖሊሲዎችን፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች እንዲሁም ወጪዎችን ሲያወጡ "ማን ይጠቅማል" የሚለውን ከግምት ማስገባታቸውን ማረጋገጥ ይችላሉ፡፡

እኩልነት ማለት ዘር፣ ገቢ፣ እድሜ፣ ችሎታና የቀደመ ታሪክን መሰረት በማድረግ ሳይለይ ሁሉም ሰው ፍትሃዊ የእድሎች፣ የመኖሪያ ቤት፣ የስራ ቦታ፣ የመጓጓዣ የማህበረሰብ ሀብቶችና የማህበረሰቡን የወደፊት እጣ ፈንታ የሚቀርጽ ድምጽ እንዲኖረው ማስቻል ነው፡፡ በአርሊንግተን ውስጥ የሚገኙ ሁሉም ማህበረሰቦች ካለፉት የእቅድና የኢንቨስትመንት ውሳኔዎች እኩል ተጠቃሚ መሆን ሳይችሉ ቀርተዋል፡፡ በእኩልነት እቅድን መንደፍ ታሪካዊ ኢፍትሃዊነትን ለማረም የሚረዳና የበለጠ ጠንካራ፣ ሁሉን ቸካታች ካውንቲ ለመገንባት ያግዛል፡፡ የበለጠ እኩልነት የሰፈነበት አርሊንግተን ማለት ለሁሉም ሰው -በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ሁኔታ የተሻለ ውጤት ማምጣት ያስችለዋል ማለት ነው፡፡

አርሊንግተን ለተለያዩ ነዋሪዎችን ድጋፍ የሚያደርጉና ሰፊ ግንኙነትንና ሁሉን አቀፍ ውሳኔ አሰጣጥን የሚያበረታቱ ጠንካራ ፖሊሲዎች፣ አገልግሎቶች እንዲሁም ፕሮግራሞች-እንደ የእኩልነት ጥራት፣ የእኩልነት መነጽርና የታለመ ኢንቨስትመንቶች ያሉት እኩልነትን ማእከላዊ ትኩረቱን አድርጓል፡፡ ሆኖም ግን በገቢ፣ መኖሪያ ቤት፣ ጤና እንዲውን ውክልና ላይ የማያቋርጥ ልዩነቶች ተጨማሪ የመኖሪያ ቤትና የሕጻናት እንክብካቤ አስፈላጊነትን፣ የበለጠ ጠንካራ መረጃን፣ መዋቅራዊ ኢፍትሃዊነትን ለመፍታት ሽርክናና ዘላቂ እኩልነትን ለማስፈን የህብረተሰቡን እምነት ማጠናከር አስፈላጊነት ያመላክታሉ፡፡

በአርሊንግተን ውስጥ እኩልነት በሚከተሉት መንገዶች ሊረጋገጥ ይችላል፡

- ያልተወከሉ ድምጾች ጋር አካታች የሆነ ተሳትፎ
- ለተለያዩ የገቢ ደረጃዎች እድሎችን የሚያቀርቡ ተመጣጣኝነት ያላቸው የመኖሪያ ቤት ስልቶች
- ውስን አማራጮች ባሉባቸው አካባቢዎች የመጓጓዣ ማሻሻያዎች
- ብክለትን ለመቀነስና ደህንነትን ለማሻሻል ጤናና የአካባቢ እኩልነት ማቀድ
- የቋንቋ እንቅፋቶችን ማስወገድና የተሻሻለ ዲጂታል ተደራሽነት
- የእኩልነት ክፍተቶችን ለመሙላት መረጃን መጠቀም




*ለጤናማ ምግቦች፣ ለአካል ብቃት እንቅስቃሴ፣ ለመዝናኛ ተደራሽነት፣ ለጤና አጠባበቅ፣ ለአካባቢያዊ ፍትህ እና ለአስተማማኝ ሰፈሮች አቅርቦቶች የህዝብ ጤና ፍላጎቶች እውቅና መስጠትናና መፍትሄ እንዲፈለግላቸው ማስቻል*

የዓለም ጤና ድርጅት ጤናን በህመም ብቻ ሳይሆን በአካል፣ በአእምሮ እንዲሁም በማህበራዊ ህይወት ረገድ ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል መልኩ ደህንነት የተጠበቀ መሆን አለበት ሲል ይገልጸዋል። የህዝብ ጤናን ለመደገፍ የጤነኛ ማህበረሰብ መርህና አራቱ ቀደምት መርሆዎች በአንድ ላይ በመሆን ይሰራሉ። ጤናማ ማህበረሰብ ነዋሪዎች ደህንነቱ የተጠበቀ አየርና ውሃ፣ ፓርኮች እንዲሁም መዝናኛዎች በቀላሉ ማግኘት፣ በአቅራቢያ ያሉ የአካባቢ የምግብ ምንጮችና አማራጮች፣ እኩል አገልግሎት የሚሰጡ የህዝብ ትምህርት ቤቶችና የጤና አጠባበቅ ተደራሽነት ከህዝባዊ ደህንነት ፕሮግራሞች ጋር መኖራቸውን የሚያረጋግጥ ነው። የግሉ ዘርፍ እነዚህን ጠቃሚ የሕዝብ ጥቅሞች በእኩልነት ማቅረብ የማይችል በመሆኑ ክፍተቶችን በመሙላት ረገድ የመንግስት ሃላፊነት ይሆና። ለምሳሌ፣ አንዳንድ የተቸገሩ ሰፈሮች ደህንነቱ ባልተጠበቀ ወይም ጤናማ ባልሆኑ ቦታዎች፣ እንደ የተበከሉ አካባቢዎች ወይም የጎርፍ ዞኖች ውስጥ የሚገኙ ሊሆኑ የሚችሉ በመሆኑ የህዝብ ፕሮግራሞች እነዚያን አደጋዎች ለመቅረፍ እገዛን ያደርጋሉ። አጠቃላይ እቅዱ የህዝብ ጤና ስጋቶችን ለመለየትና ለመቆጣጠር እንዲሁም ጠንካራ ጤናማ የማህበረሰብ ግቦችን ለማበረታታት ጠቃሚ አካሄድ ነው።

በእቅድ ውስጥ ጤናና ደህንነት ከጤና አጠባበቅ ተደራሽነት፣ ወንጀልንና የአደጋ ጊዜ ዝግጁነትን ከማድረግ ባሻገር የሚሄድ ነው— ይህ ማለት የጤና ልዩነቶችን መቀነስና የአካል፣ የአእምሮ እንዲሁም የማህበራዊ ደህንነትን መደገፍ እንዲሁም የጎርፍ አደጋዎችንና ሌሎች ከአየር ንብረት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተጽእኖዎችን በታሰበ ንድፍና አገልግሎቶች መቀነስ ማለት ነው፡፡ የሚኖሩበት ቦታ ለምን ያህል ጊዜና ምን ያህል በጥሩ ሁኔታ እንደሚኖሩ በማሳየት ረገድ ተጽእኖ ይኖረዋል፡፡ ደህንነቱ የተጠበቀ መኖሪያ፣ ንጹህ አየር፣ በእግር የመሄጃ መንገዶች፣ መናፈሻዎችና ጤናማ ምግብ ያላቸው ማህበረሰቦች የተሻለ የጤና ውጤት የሚያስገኙ ናቸው፡፡

አርሊንግተን ጠንካራ የሆነ የህዝብ ጤና ስርአቶች፣ የአደጋ ጊዜ እቅድና የማህበረሰብ ፕሮግራሞች ለመዝናናት፣ ለችግሮች ምላሽ መስጠትና ደህንነትንና መቻልን የሚደግፉ የምግብና የመኖሪያ ቤት ድጋፎች አሉት፡፡ አሁንም በጤና፣ በምግብ ዋስትናና በመኖሪያ ቤቶች ረገድ ያሉ ልዩነቶች — ያረጁተቋማት፣ የአየር ንብረት ተጽእኖዎችና ውስን ሀብቶች — ትብብርና ፈጠራን የሚጠይቁ ቀጣይ ተግዳሮቶችን ይፈጥራሉ፡፡

በአርሊንግተን ጤናማና ደህንነቱ የተጠበቀ ማህበረሰብ በሚከተሉት መንገዶች ሊገኝ ይቻላል፡

- ደህንነትን የሚያሻሽል፣ የጉዳት አደጋን የሚቀንስና ማህበራዊ ትስስርን የሚያበረታታ መንደፍ
- ማህበረሰቡ ኢኮኖሚውን ለማሻሻል በአገልግሎቶች መስጫ አቅራቢያ የተደረገ አስተማማኝ፣ ተመጣጣኝ መኖሪያ ቤት
- ንጹህ አየርና ውሃ እንዲሁም የተሻሻለ የድምጽ ደንቦች
- ወቅቱን የጠበቀ ምግብ በገበሬዎች ገበያዎች፣ ግሮሰሮችና የከተማ ግብርና ማግኘት
- በእግር ለመሄድ፣ ብስክሌት ለመንዳት የሚያስችሉ ሰፈሮች
- ለፓርኮች፣ መዝናኛና ክፍት ቦታ ተደራሽ መሆን

**የእርስዎን አስተያየት እንፈልጋለን**

የእርስዎ ድምጽ የመግቢያውን ምእራፍ ለመቅረጽ ይጠቅማል! የእርስዎን አስተሳሰቦች፣ ሃሳቦችና ስጋቶች መስማት እንፈልጋለን፡፡

ግምረመልሶችዎን እዚህ ጋር ያጋሩ፡፡

በአካልና በኢንተርኔት ላይ በሚካሄዱ ስብሰባዎች እንዲሁም ዝግጅቶች በዚህ የበልግ ወቅት ይካሄዳሉ፡፡ ክትትል በማድረግ ተሳትፎዎን ይቀጥሉ፡፡